ምድብ አምስት (ከ10ኛ — 12ኛ) ክፍል

14 ኛ ሳምንት

# ምሥጢረ ተክሊል

**የቃሉ ትርጉም፡-** ከለለ፣ አከበረ - ተክሊል ክብር ማለት ነው፡፡

**ተክሊል፡-** ሙሽራ እና ሙሽሪት ከሁለት አንድ የሚሆኑበትና መለኮታዊውን ጸጋ የሚያገኙበት ምሥጢር ነው፡፡

- የጋብቻ አንድነት የሚቀደስበትም ነው፡፡ የዚህም ፍጹም አንድነትና መንፈሳዊነት እንደ ክርስቶስና ቤተክርስቲያን አንድነት ነው፡፡ኤፌ.5:31-32
- ይህም ምሥጢር ትልቅ ጥቅም አለው፡፡ የሁለት ሰዎች ሕይወትና ጉዳይ ብቻም አይደለም መንግሥት፣ቤተክርስቲያንና የእግዚአብሔር መንግሥት በጥልቀት የሚሳተፉበት ነው፡፡ በቀላሉ የምንመለከተው ወይም በግዴለሽነት የምንፈጽመው አይደለም፡፡

አመሠራረቱ፡- ጋብቻ ዓለም ሲፈጠር በእግዚአብሔር ተመሥርቷል፡፡ ***«እግዚአብሔር ሰውን በመልኩ ፈጠረ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው ወንድናሴት አድርጎ ፈጠራቸው እግዚአብሔርም ባረካቸው እንዲህም አላቸው ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት ግዙአትም»*** ዘፍ.1÷27-28

**በሐዲስ ኪዳንም ክርስቶስ ይህን ምሥጢረ አረጋግጦልናል**

- በቃና ዘገሊላ ሠርግ ላይ በመገኘት /ዮሐ 2:1-11/
- በትምህርት ***«ስለዚህ ሰው አባቱን እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንደ ሥጋ ይሆናሉ ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደፊት ሁለቱ አይደሉም እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው»*** ማቴ 19÷ 4- 6

**የጋብቻ ዓለም ሦስትናቸው፡-**

1. **ለመባዛት** የሰውን ዘር ለመጠበቅና ለማስፋት ***«ብዙ ተባዙ ምድርን ሙሉአት»*** ዘፍ.1-÷28 የሰው ዘር መብዛትም የቤተክርስትያን መስፋት ነው::
2. **ለመረዳዳት** «***ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት***» ዘፍ. 2-÷18
3. **ከዝሙት ለመጠበቅ** በሰው ልጅ ውድቀት ኃጢአት ወደ ዓለም ከገባ በኂላ ጋብቻ ከሥጋዊ ፍትወት መጠበቂያ ሆኗል፡፡

«***ስለጻፋችሁልኝስ ነገር ከሴት ጋር አለመገናኘት ለሰው መልካም ነው ነገር ግን ስለዝሙት ጠንቅ ለእያንዳንዱ ለራሱ ሚስት ትኑረው ለእያንዳንዲቱ ደግሞ ለራስዋ ባል ይኑራት ሳላገቡና ለመበለቶች ግን እላለሁ እንደእኔ ቢኖሩ ለእነርሱ መልካም ነው ነገር ግን በምኞት ከመቃጠል መጋባት ይሻላልና ራሳቸውን መግዛት ባይችሉ ያግቡ*** »1ኛ.ቆሮ.7÷19

**የቅድመ ጋብቻ ዝግጅቶች፡-**

**የሕይወትን መስመር መምረጥ** በምንኩስና ወይም በሕግ ለመወሰን መርጠን በጊዜ መወሰን ከዚያም በወሰንነው የሕይወት መስመር መኖር፡፡ክርስቲያኖች ከሁለቱ የወጣ ኑሮ የላቸውም፡፡ «***እያንዳንዱ ከእግዚአብሔር ለራሱ ስጦታ አለው አንዱ እንደዚህ /ምንኩስና/ ሁለተኛውም እንደዚያ /በጋብቻ/፡፡»***1ኛ.ቆሮ.7:7 በተጨማሪም ማተ.19:12

***መተጫጨት*** በሁለት ተጋቢዎች መካከል በፈቃዳቸው የሚፈጸም መምረጥ መፈቃቀድ መስማማት ማለት ነው፡፡በዚህ የመተጫጫት ወቅትም ፍቅር ሃይማኖት ተመጣኝ ብስለት ይጠበቃል ፍቃደ እግዚአብሔርን ማስቀደምና መጠየቅ የመጽሐፍ ትምህርት ነው፡፡

አንድ ሰው ለወደፊት ሕይወቱ ረዳት የሚሆነው ወይም የሚሆናትን ጓደኛ ለማግኘት ፈቃደ እግዚአብሔርን ሊጠይቅ /ልትጠይቅ/ ይገባል፡፡ አስተዋይ የትዳር ጓደኛ የሚሰጥ እግዚአብሔር ብቻ ነውና፡፡

**ፈቃደ እግዚአብሔርን እንዴት ማወቅ ይቻላል**

- **በጸሎት** ፍቃደ እግዚአብሔር በጸሎት እንደሚታወቅ ጌታችን «***ወይኩን ፈቃድከ***» ማተ 6:10 ብለን እንድጸልይ አስተምሮናል:: ዘፍጥ.24:13-14፣ማተ7:7-12
- **በማስተዋል** ***«ሰውየውም ትክ ብሎ ይመለከታት ነበር፤እግዚአብሔር መንገዱን አቅንቶለት እንደሆነ ወይም እንንዳልሆነ ለማወቅም ዝም አለ፡፡»*** ዘፍጥ.24:21
- **በምክረ ከህን በመመራት** የነፍስ አባቶቻችንን በማማከር መንፈሳዊ ሕይወታችንን ከፈተናዎች እንጠብቃለን፡፡
- **በቃለ እግዚአብሔር በመመዘን** ቃለ እግዚአብሔር የእግዚአብሔርን ፍቃድ የምናውቅበት፤የክፉውን ፍላጻ የምናሸንፍበት ኃይል፤ኤፌ.6:16-17 ነው፡፡ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ሲስማማ ፍቃደ እግዚአብሔርን ያስረዳናል፡፡እግዚአብሔር ለወዳጆቹ መልካም ያልሆነ ነገር አይሰጥምና፡፡ ዘፍ. 24

ከቅዱስ ቃሉ ጋር የሚጋጭ ማንኛውም ነገር ግን ከእግዚአብሔር እንዳልሆነ እንረዳለን፡፡***«ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ..........ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን»*** ተብለናልና ***ገላ.1:8 ፕ 9*** በተጨማሪም ***«ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል፡፡ዝናብም ወረደ ጎርፍም መጣ ነፋስም ነፈሰ፤ያንም ቤት ገፋው በዓለት ላይም/ቃለእግዚአብሔር/ስለተመሠረተ አልወደቀም፡፡»***ማተ7:24-25 ቤታችን በቃለ እግዚአብሔር ላይ ከተመሠረተ በፈተናዎች አይወድቅም

- **በእውነተኛ ፍቅር** ስሜታዊ ያልሆነና በእውነተኛ ፍቅር ላይ የተመሰረተ መሆኑን ከላይ በተጠቀሱት መሰረት መመዘን፡፡

ስሜታዊ ፍቅር ግን ውጤቱ ኃጢአት ነው፡፡የኃጢአት መጨረሻው ደግሞ ከእግዚአብሃሔር መለየት/ሞት/ ነው፡፡2ኛ ሳሙ.13፡1-29፤ያዕ.1፡15

**በመተጫጨት ጊዜ ሊሟሉ /ሊጤኑ/ የሚገባቸው ነገሮች**

1. የሃይማኖት አንድነት ዘዳ.7፡3-4፣1ኛ.ነገ.11፡1-8፣1ቆሮ. 15፡33፣ መዝ. 17፡25
2. ለአቅመ አዳምናሄዋን ከልደረሱ መተጫጨት ክልክል ነው ጋብቻቸው አይጸናልም
3. ተቀራራቢ.አመለንከተበመንፈሳዊህይወት፤በማህበራዊ ጉዳይ፤በእውቀት/ትምህርት/፡፡
4. ዝምድና የሌላቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡ ዝምድና ሦስት መልክ አለው ስጋዊ ዝምድና፣ መንፈሳዊ ዝምድና፣ የጋብቻ ዝምድና

   1. ሥጋዊ ዝምድና፡- በተጋቢዎች መካከል እስከ ሰባት ትውልድ ድረስ ዝምድና እንዳይኖር በሥርዓተ ቤተክርስቲያን ተደንግጓል፡፡ ፍት. ነገ. 28፡842

      ሀ. የአባቱን የአያቱን ሚስት፣ ልጅ፣ እህት፣ እናት አይገባም፡፡

      ለ. የልጁን ሚስት፣ ልጇን ፣ እህቷን አያገባም፡፡

      ሐ.የወንድሞቹንናየልጃቸውን ሚስት፣ልጇን፣እህቷን፣አያቷን አያገባም፡፡

      መ.በተጨማሪ የጡት ልጅ፣እናትናአባት እንደልጁ ካሳደጉት/ጓት/ መተጫጨት መጋባት ክልክል ነው፡፡

   2. መንፈሳዊ ዝምድና፡- የክርስትና ዝምድና ማለት ነው፡፡

      ሀ. የክርስትና አባቱን ሚስት፣ እህት፣ ልጅ፣ የልጅ ልጅ፣ እህት አያገባም፣

      ለ. የክርስትና ልጁን እናት፣ እህት፣ የእህት የወንድም ልጁን አያገባም፡፡

   3. የጋብቻ ዝምድና፡-ባል የሚስቱን አያት፣ እናት፣ አክስት፣ አጎት፣ ልጇን፣ የልጅ ልጇን አያገባም ሚስትም እንዲሁ፡፡

**የጓደኝነትን /የእጮኝነትን/ ጊዜ እንዴት ማሳለፍ ይገባል**?፡- የእጮኝነት ጊዜ የጋብቻ ጊዜ እንዳልሆነ አውቆ የተቃራኒ ፆታ ግንኙነቶችን ሳይደረግ ሰፋ ባለ መልኩ በቃልና በሀሳብ የሚተዋወቁበትን ጠባይ ለጠባይ የሚጠናኑበትን ወደፊትም በትዳር ውስጥ ሊገጥማቸው የሚችሉትን ነገሮች በዚህ ጊዜ የሚፈቱበት ስለጠባያቸው ባለመተፋፈር የሚነጋገሩበት ጊዜ ነው፡፡ይህ ጊዜያቸውን ከፈጸሙ በኋላ ቤተሰባቸውን በተለያየ መንገድ ግንኙነታቸውን እንዲያውቁ ማድረግ አለባቸው፡፡

**የእጮኝነት ጊዜ ቅድስናን /ክብረ ንፅህናን ማጣት/ እንዴት ይመጣል**?

1. የእጮኝነት ጊዜ በማራዘም
2. መገናኛ ቦታን ባለመምረጥና በመሸሽ /በመደበቅ/
3. ከቃለ እግዚአብሔር በመራቅ

**በእጮኝነት ጊዜ የሚፈፀሙ ግንኙነቶችን ለመከላከል የሚያስችሉ መንገዶች**

ሀ. ሁለቱ እጮኛሞች ሰው የሌለበት ቦታ በመሆን መዳራት አይገባቸውም 1ኛ ጴጥ. 4፡1 1ኛ ጴጥ 2፡2 ሲራክ 9፡5 ምሣ. 6፡29

ለ. ፍቃደ ስጋን የሚያነሳሱ ህሊናን ወደማያስፈልግ ግንኙነት የሚያመሩ ጽሁፎችን አለማንበብ፣ፊልሞችን፣ ዘፈኖችን፣ ቀልዶችን፣ አለማድመጥና አለማየት፡፡

መ. በአብዛኛው ወደ ጸሎትና ወደ ቃለ እግዚአብሔር ሐሳባቸውን ማዘንበል፡፡

ሠ. የዝሙት ፈተና በተነሳባቸው ጊዜ መጸለይና መስገድ አለባቸው፡፡

ረ. አለመፍረድ በተቀደሰ ጋብቻ የሚኖሩትን የእድሜ ባጸጎችን ማክበር፤አርዓያ ማድረግ፡፡

ሰ. የንስሐ አባትን ማማከር፡፡

**በተክሊል ለመጋባት የተጋቢዎች መመዘኛ**

1. ሁለቱም ተጋቢዎች ድንግል መሆን ለባቸው፡፡ እዚህ ላይ ግን ዝሙት ሳይፈጽሙ ድንግልና ባይገኝባቸው ከተክሊል የማይከለከሉ አሉ፡፡ እነዚህም፡-

   ሀ. በህክምና ምክንያት ድንግልናቸውን ለሚያጡ

   ለ. በተፈጥሮ ሲወለዱ ድንግልና የሌላቸው ሰዎች አሉ /-3%/ እነዚህ ተክሊል አይከለከሉም፡፡

   ሐ. የመደፈር አደጋ ያጋጠማቸውና ፈልገውና አውቀው የሠሩት የዝሙት ኃጥአት ከሌለ ተክሊል አይከለከሉም፡፡

   መ. ከብዙ እንቅስቃሴና ከበድ ያለ ሥራ ከመስራታቸው የተነሳ ድንግልናን ማጣት ያጋጥማልና ተክሊል አይከለከልም፡፡

2. ሁለቱም የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ምእመን ሆነው የንስሐ አባት ይኖራቸዋል፡፡
3. ጋብቻ የሚከለክሉትን ስጋዊና መንፈሳዊ ዝምድናን፣ የአዕምሮ ጉድለት፣ ከመጠን በላይ የሆነ የእድሜ መበላለጥ በተጋቢዎች መካከል መኖር የለበትም፡፡

4. ሁለቱም ስተክሊል ጋብቻ ዝግጁዎች ፈቃደኞች መሆን ይገባቸዋል፡፡ በመተጫጨት ጊዜ ማሳለፍ የሚገባቸውን ነገር ማሳለፍ አለባቸው፡፡

**ጥሎሽ**

ጥሎሽ ፍቅርን መግለጫ ስጦታ ሲሆን የተጀመረውም በአዳምና ሔዋን ነው፡፡ የአዳም ጥሎሽ ወርቅ፣ ዕጣን፣ ከርቤ ነበር፡፡ የሰጠውም እግዚአብሔር ነው፡፡

የአብርሃም አገልጋይ ኢያውብርስ ለይስሐቅ ሚስት ጥሎሽ ይዞ ነበር፡፡ ፍት.ነገስትም ጥሎሽ እንዲሰጥ ያዛል፡፡ ጥሎሽ ፍቅርን መግለጫ እንጂ እዳ አይደለም፡፡ ሁሉም እንደ አቅሙ በመጠን ሲሆን ይገባዋልና፡፡

**የቃል ኪዳን ቀለበት**

እስከ ሞት ድረስ የማይፈርስ ፍጻሜ የሌለው በመሆኑ ተጋቢዎች እስከ መጨረሻው አብረን እንኖራለን ሲሉ በክብነት ፍፃሜ የሌለውን ቀለበት ያስራሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቀለበት ፍቅርን፣ ክብርን፣ ይገልፃል፡፡ መኃ. 8፡6 ስለዚህ ለፍቅር ምልክትና ስለመዋሃዳቸው ተጋቢዎች ቀለበትን ያስራሉ፡፡ ቃል ኪዳን በሁለቱ ተጋቢዎች መካከል የሚፈጸም የሚጸና የማይናወጥ መሀላ ሲሆን ቃል ኪዳን ካህን ፊት ይፈጸማል፡፡ ስለዚህ ጋብቻ ለጊዜው ተባብሮ የመኖር ዘዴ ሳይሆን እስከ ሞት ድረስ የማይፈርስ ላከበሩት የሚያከብር መንፈሳዊ ፀጋን የሚያስገኝ የሕይወት ማዕረግ ነው፡፡

**ጋብቻ አንድ ወንድ ከአንድ ሴት ጋር ነው**

ማንኛውም የሰው ልጅ ከአንድ በላይ ማግባት እንደማይገባው ከመጀመሪያዎቹ ሰዎች ከአዳምና ከሄዋን መማር ይቻላል፡፡ ከአንድ በላይ ማግባት የሚፈቀድ ቢሆን ሁለት ወንድ ለሔዋን ሁለት ሴት ለአዳም በተፈጠረላቸው ነበርና፡፡ ዘፍ. 1፡27 ማቴ፣ 19፡9

**የባልና ሚስት ግዴታዎች**

**ከጋብቻ በፊት፡-**

1. ሁለቱም ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን መሆነ አለባቸው፣ ምክንያቱም የክርስቶስ ፀጋ ክርስቲያን ላልሆኑ አይሠጥምና፡፡
2. መንፈሳዊ እና ሥጋዊ ዝምድና ሊኖራቸው አይገባመ
3. እያነዳንዳቸው ሌላውን ለማግባት ሙሉ ፈቃደኞች መሆን አለባቸው የቤተሰብ ፍላጎት ብቻ በቂ አይደለም ካህኑ እያንዳንዳቸውን በየግል ሊጠይቃቸውና በግልጥ መፍቀዳቸውንም ማሳወቅ አለባቸው፡፡
4. ቅድመ ጋብቻ ከሩካቤ ሊጠበቁም ይገባቸዋል፡፡

**በጋብቻ ጊዜ፡-**

1. ተክሊል አንድ የቤተክርስቲያነ ምሥጢር እንደመሆኑ ጋብቻ መፈጸም ያለበት በቤተክርስቲያን ነው ይሄንን ማስተማርና መምራት ያላባቸውም ካህናት ናቸው
2. ምሥጢሩን ለመፈቃቀድም መገኘት ያስፈልጋል
3. የቤተክርስቲያን ጋብቻ በግልጥ ይደረጋል በቤተክርስቲያን፡፡

**ከጋብቻ በኂላ፡-**

1. ባል አንድ ሚስት ብቻ ሊኖረው ይገባል፡፡ ሚስትም አንድ ባል ብቻ ሊኖራት ይገባል፡፡ ማቴ. 19÷ 45
2. አንዳቸው ቢሞቱ በሕይወት ሥጋ ያለው /ያለችው /ማግባት ይችላሉ::1ኛ. ቆሮ. 7÷ 39
3. ከዝሙት በስተቀር መለያየት የለባቸውም ማቴ. 19÷ 6-9
4. ባል ለሚስቱ የሚገባትን ሁሉ መፈጸም ይገባዋል፡፡ ሚስትም ለባሏ እንዲሁ 1ኛ ቆሮ. 7፡3
5. ለጾምና ለፀሎት ከተወሰነ ጊዜ በስተቀር ሰይጣን ድል እንዳይነሳቸው መለያየት የለባቸውም፡፡ 1ኛ ቆሮ. 7፡5-6
6. ቤተክርስቲያን በክርስቶስ እንደምትታዘዝ ሚስትም ለባሏ መታዘዝ ይገባታል እንዲሁም ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳት ባል ሚስቱን መውደድ መርዳት ይገባዋል፡፡ ኤፌ. 5፡2-33፣ 1ኛ ጴጥ. 3፡7
7. በመተማመን በአንድ ሀሳብ በአንድ ልብ ሆነው መኖር አለባቸው1ኛ. ጴጥ. 3፡8
8. ባልና ሚት በጽንስ፣ በርሕስ፣ በትክትክ፣ በሰንበት፣ በበዓላት፣ በአጽዋማት ከሩከቤ ሥጋ መጠበቅ ይገባቸዋል፡፡

**ፍቺ**

ሀ. በሥርዓተ ተክሊል ባልና ሚስት ጋብቻ ከፈጸሙ መፈታት አይገባም፡፡ ማር.10፡29፣ 1ኛ ቆሮ. 7፡27 ትን.ሚል. 21፡16፣ ቆሮ. 11፡11

ለ. ባልና ሚስት በድንገተኛ ግጭት ቢለያዩ እንኳ መታረቅ አለባቸው፡፡አንታረቅም ካሉ ሌላ ማግባት አይችሉም ንጽኅናቸውን ጠብቀው መኖር አለባቸው፡፡ 1ኛ ቆሮ. 7፡10-11

ሐ. መፍታት የሚቻለው በዝሙትና በሞት ምክንያት ብቻ ነው፡፡ 1ኛ ቆሮ. 7፡39፣ ማቴ. 5፡32

መ. ሰነፊች፣ መከነች፣ደኸየች ብሎ መፋታት አይገባም። ይኸውም በሥርዓተ ተክሊል ጊዜ በመሐላ ቃል የምንገባው ነው።

<u>ሁለተኛ ጋብቻና መአሰባን</u>

***መአሰባን*** አግብተው የፈቱ ማለት ነው። እነዚህ በንጽህና መኖር ከልቻሉ ማግባት ይችላሉ።ሁለተኛ ጋብቻ ከመፈጸሙ በፊት ካህኑ የቀድሞ ጋብቻ ለምን እንደፈረሰ ይመረምራል። ወደፊትም እንደማይፈርስ አረጋግጦ ሥርዓቱን ይፈጽማል። ለሁለተኛው ጋብቻ ሥርዓተ ተክሊል አይደረግም ፍትሐት ዘወልድና የንስሐ ጸሎት ተደርጎ በቅዱስ ቁርባን ጋብቻቸውን ይፈጽማሉ።

<u>ሦስተኛ ጋብቻ</u>

ሦስተኛ ጋብቻ ፈጽሞ የተናቀ ነው። ነገር ግን አንድ ሰው ለሦስተኛ ጊዜ ጋብቻን ለመፈጸም ቢፈልግ በቤተክርስቲያን ሕግ መሰረት የንስሐ ጸሎት ተደርሶለት ጋብቻውን ይፈጽማል ፤ከሦስተኛ በላይ ጋብቻ ለክርስቲያን አልተፈቀደም።

<u>ከአንዴ በላይ ማግባት የሚችሉት እነማን ናቸው?</u>

1. ባል /ሚስት/ የሞተባቸው
2. በዝሙት ምክንያት

<u>ጋብቻ እንዴት ይፈጸማል?</u>

ጋብቻ በቤተክርስቲያን በሥርዓተ ተክሊል፣ በመአሰባንና በቅዱስ ቁርባን ቤተሰብና የንስሐ አባት በተገኙበት የፈጸማል።

<u>ሥርዓተ ተክሊል</u>

1. ጋብቻ ያለ ስርዓተ ተክሊል አይፈጸምም
2. ሥርዓተ ተክሊል ድሣና ባለጸጋ ፣ ካህንና ምእመን የማይሉበት በድንግልና ለኖረ ሁሉ የሚፈጸም ነው።
3. ሥርዓተ ተክሊል በስጋ ወደሙ ይጸናል። ያለ ስጋ ወደሙ አይፈጸምም።

<u>የሚታይ ምልክት፡-</u>

- ተጋቢዎች በቤተክርስቲያን ፊት የሚፈጽሙት ቃለ መሐላ
- ሥርዐተ- ተክሊሉና ጸሎቱ
- የሚቀቡት ቅብዐት ሲሆኑ
- የጋብቻው አንድነት መቀደሱና መንፈሳዊ መሆኑ "መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን" ዕብ 13÷ 4 "ይህ የእግዚብሔር ፈቃድ እርሱም መቀደሳችሁ ነውና ከዝሙት እንድትርቁ እግዚአብሔርን እንደማያውቁ አሕዛብ በፍትዎት ምኞት አይደለም እንጂ ከእናንተ እያንዳንድ የራሱን ዕቃ በቅድስናና በክብር ያገኝ ዘንድ" 1ኛ. ተሰሎ. 4÷ 3-5
- አንደነት ሁለቱ አንድ የሚሆኑበትና የማይለያዩበት ጥበቃና እርዳታ ማግኘታቸው ሲሆን ይህም የክርስቶስና የቤተክርቲያን አንድነት አይነት ነው እግዚአብሔር ያጣመረውን ሰው አይለየው ማቴ. 19÷ 6
- ባልና ሚስት እርስ በርስ የሚተማመኑ ማድረግ

<u>በሚስጥረ ተክሊል የማይታይ ፀጋ</u>

1. ሁለትነት ጠፍቶ አንድነት ሲፀና ዘፍ. 2፡22፣ ኤፌ. 5፡32
2. እስከ ሞት እንዳይለዩ የሚያበረታታ መንፈሳዊ ፀጋ
3. የመተማመን የመረዳዳት ፀጋ
4. መልክም ፍሬ ለማግኘት መንፈሳዊ ፀጋ መዝ. 12፡126.5፣ ዕብ. 13፡4

በሚስጥረ ተክሊል ሙሽራውና ሙሽሪቱ የሚለብሱት ልብስ እንደ ክብር የሚወርሱ ሁለትነት ቀርቶ አንድ አካል መሆናቸውን የሚያመለክት ነው። የሚቀዳጁት አክሊልም የሚያገኙትን ክብር የሚያመለክት ነው። ቀለበቱ የሃይማኖት የክብር ባል በሚስቱ ሚስት በባሏ የታሰሩ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው።

<u>ጋብቻን ስለሚቃወሙ ሰዎች</u>

በመጀመሪያ ምዕተ አመት የተነሱ ግኖስቲኮች የተባሉ መናፍቃን "ጋብቻን የሰይጣን ስራ ነው በዚህ ዓለም መውለድ መራባት ኃጢአት ማብዛት ነው" እያሉ ያስተምሩ ነበር። ነገር ግን ጋብቻ ቅዱስ ነው። 1ኛ ጢሞ. 4፡3 ዕብ. 13፡4 ኤፌ 5፡32 ጌታችንም በመዋዕለ ስጋዊው ስለ ጋብቻ ቅዱስነት ተናግሯል። ጋብቻ እርኩስ ቢሆን ኖሮ ንፁህ ባህርይ የሆነ አምላክ በአካል ተገኝቶ በሰርግ ቤት ጋብቻን ባልባረከ ነበር። ዮሐ. 2፡1-10፣ ማቴ 19፡3-6 ስለዚህ ጋብቻን የሚቃወሙ ሁሉ ከክርስቶስ የወጡ ከቤተክርስቲያንም የተለዩ ናቸው። «***እኛስ ጋብቻ ቅዱስ እንደሆነ ልደትም ርኩሰት እንሌለበት እንናገራለን ሕዝቡ ይበዙ ዘንድ እግዚአብሃሔር አዳምንናሔዋንን ፈጥሮዋልና*** »አመክንዮ ዘሐዋርያት

**ይቆየን።**